መልእክት አምስት

**ለከፉ ዓላማቸው የትምህርት ነፋሳት ውስጠ-መሠረታዊ አስተዋጽኦ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦- ኤፌ. 4፡13-15፤ ሐዋ. 2፡42፤ 1 ጢሞ. 1፡3-4፤ ቲቶ. 1፡9፤ 1 ቆሮ. 1፡2፤ 4፡17፤ 12፡12-13፡27

I. **የሐዋርያት ትምህርት የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ልዩና-ብቸኛው እና ጤናማው ትምህርት ነው—ሐዋ. 2፡42፤ 1 ጢሞ. 1፡3-4፤ 6፡3፤ ቲቶ 1፡9፤ 2፡1፦**

ሀ. የሐዋርያት ትምህርት ለአዲስ ኪዳን ሕዝቡ እግዚአብሔር በልጁ የተናገረው የመላው አዲስ ኪዳን ትምህርት ነው—ዕብ. 1፡1-2።

ለ. የሐዋርያት ትምህርት ከእግዚአብሔር ተሠግዎ እስከ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም መጠናቀቅ ድረስ የእግዚአብሔር አዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ ልዩና-ብቸኛው፣ መለኮታዊው መገለጥ ነው—ዮሐ. 1፡14፤ ራእ. 21፡2።

ሐ. የሐዋርያት ትምህርት በአንድ ልብ የመሆን ዋናው ነገር ነው፣ አንድ ልብ፣ አንድ መንገድ እና አንድ ግብ እንዲኖረን የሚያደርገን ነው—ሐዋ. 1፡14፤ 2፡42፣ 46፤ ኤር. 32፡39።

መ. "በሐዋርያት ትምህርት መሠረት የሆነውን የታመነውን ቃል የምናምን"[1] መሆን አለብን—ቲቶ 1፡9፦

1. አብያተ ክርስቲያናት የተመሠረቱት በሐዋርያት ትምህርት መሠረት ነበር፣ ትምህርታቸውንም ተከተሉ፣ እንዲሁም የአብያተ ክርስቲያናት ስርዓት ተጠብቆ የቆየው በሐዋርያት ትምህርት መሠረት በተሰጠው በታመነው ቃል ነበር።
2. ከጤናማው የሐዋርያት ትምህርት፣ ከእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ትምህርት ጋር የሚስማሙ ነገሮችን መናገር አለብን—2፡1፣ 7-8፤ 1 ጢሞ. 1፡4።

ሠ. ከሐዋርያት ትምህርት ልዩ የሆነ ማንኛውም ትምህርት በሐዋርያት አይፈቀድም ነበር፤ "ልዩ ትምህርቶችን" ማስተማር የተከለከለ ነበር—ሐዋ. 2፡42፤ 1 ጢሞ. 1፡3-4፦

1. *ልዩ ትምህርት* ከእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ጋር ስምም ያልሆኑ ትምህርቶችን ያመለክታል—6፡3።
2. በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት አልበኝነት በዋነኛነት የሚከሰተው ከሐዋርያት ትምህርት ዘወር ከማለት ነው—ሐዋ. 2፡42።
   ሀ. ይህንን ለመቃወም፣ በሐዋርያት ትምህርት መሠረት በአብያተ ክርስቲያናት የሚሰጠውን የታመነውን ቃል ትምህርት ማመን አለብን—ቲቶ. 1፡9።
   ለ. በጨለማ በተደረገ እና ግራ በተጋባ ሁኔታ ውስጥ፣ በአዲስ ኪዳን ካለው አብርሆት ከሚሰጠውና ስርዓት ከሚያሲዘው ቃል—ከሐዋርያት ትምህርት—ጋር መጣበቅ ያስፈልገናል—ሐዋ. 2፡42።
3. ልዩ ትምህርቶችን መተው እና ስለ ክርስቶስ እና ቤተ ክርስቲያን በሆነው በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ላይ ማተኮር አለብን—1 ጢሞ. 1፡3-4፤ ኤፌ. 3፡9፤ 5፡32።

ረ. ሐዋርያው ጳውሎስ በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት አንድ አይነት ነገርን አስተማረ፤ እኛም በምድር ሁሉ በእያንዳንዱ አገር ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ውስጥ አንድ አይነት ነገርን ማስተማር አለብን—1 ቆሮ. 4፡17፣ 7፡17፤ ተዛ. ቆላ. 4፡16።

ሰ. የሐዋርያዊው አገልግሎት ጤናማ ትምህርት ዋናው ነጥብ የሚያተኩረው ሦስታንዱ አምላክ ራሱን ሁሉን-እንዳካተተው ሕይወት-እንደሚሰጠው መንፈስ ወደ መረጣቸው ሰዎች ውስጥ ለማደል በሂደት ማለፉን ነው፣ ይኸውም መለኮታዊውን መተላለፍ ለመቀበል ወደ ሕይወታዊ ጥምረት ውስጥ ይመጡ ዘንድ እና የእግዚአብሔር ልጆች እና የክርስቶስ ብልቶች ይሆኑ ዘንድ ነው፤ በውጤቱም፣ የእግዚአብሔር ሙላት የሚያድርበትን ክርስቶስ ለመግለጥ የክርስቶስ አካል መሆን ይችላሉ—1 ቆሮ. 15፡45፤ 6፡17፤ 12፡12-13፤ 27።

ሸ. ከእግዚአብሔር አዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ ልዩና-ብቸኛ መገለጥ ልዩ የሆኑ ትምህርቶች ሁሉ በሐዋርያት የትምህርት ነፋሳት ተብለው ይቆጠራሉ—ኤፌ. 4፡14።

II. **ከእንግዲህ ወዲህ "በማዕበል ወደ ፊትና ወደ ኋላ እየተነዳን፣ በልዩ ልዩ አይነት የትምህርት ነፋስ፣ በሰዎችም ረቂቅ ተንኮልና ማታለል ወዲያና ወዲህ እየተንገዋለልን ሕፃናት" መሆን አይገባንም—ቁ. 14 (አ.መ.ት.)።**

ሀ. *ሕፃናት* በክርስቶስ ልጆች የሆኑትን፣ የሕይወት ብስለት የጎደላቸውን አማኞች ያመለክታል—1 ቆሮ. 3፡1፤ ኤፌ. 4፡13፣ 15።

[1] ከእንግሊዝኛው ሪከቨሪ ቨርዥን መጽሐፍ ቅዱስ በቀጥታ የተተረጎመ

ለ. ማዕበሎቹ የሚነሳሱት አማኞችን በማባበል ከክርስቶስ እና ከቤተ ክርስቲያን ጠራርጎ ለመውሰድ በልዩ ትምህርት ነፋሳት፣ በአስተምህሮዎች፣ በጽንሰ-ሃሳቦች እና በሰይጣን በተላኩ አመለካከቶች ነው—1 ጢሞ. 1፥3-4፤ ኤፌ. 4፥14፦
1. በክርስቶስ ሕፃናት ለሆኑ እነዚህን መለየት አስቸጋሪ ነው፤ በትምህርት ነፋሳት ከሚነሳሱ ማዕበሎች የማምለጫው ብቸኛ መንገድ በሕይወት ማደግ ነው፣ በሕይወት ለማደግ አስተማማኙ መንገድ በክርስቶስ እና በቤተ ክርስቲያን ጥበቃ በተገቢው የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ መቆየት ነው—ቁ. 13-15።
2. የአማኞችን ትኩረት ከክርስቶስ እና ከቤተ ክርስቲያን ዘወር የሚያደርግ ማንኛውም ትምህርት፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውም እንኳን ሳይቀር ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዓላማ የሚወስዳቸው ነፋስ ነው—ቁ. 14።

ሐ. የትምህርት ነፋሳትን ውስጠ-መሠረታዊ መሠረት ማየት ያስፈልገናል—ቁ. 14፦
1. ውስጠ-መሠረታዊ መሰረት ስውር መሠረት፣ በግልጽ የማይታይ መሠረት ነው።
2. ይህን ውስጠ-መሠረታዊ መሠረት ለማየት፣ ወደ መላው ሁኔታ ውስጥ ዘልቆ መግባት የሚችል ተገቢ እና የሰላ መረዳት ያስፈልገናል።
3. እነዚህ ትምህርቶች ከአዲስ ኪዳን ትምህርት ማለትም ለክርስቶስ አካል መገንባት ከሆነው ከእግዚአብሔር ኢኮኖሚ የተለዩ ናቸው—1 ጢሞ. 1፥3-4፤ 6፥3፦
   ሀ. እያንዳንዱ የትምህርት ነፋስ መልካም ይመስላል፤ ሆኖም ግን፣ ውስጠ-መሠረታዊ በሆነ መልኩ በትምህርት ነፋሳት ውስጥ ከሐዋርያት ትምህርት ልዩ የሆነ ነገር አለ፣ መልካምም አይደለም።
   ለ. የትምህርት ነፋሳት የአማኞችን እምነት ይገለብጣሉ የቤተ ክርስቲያን ሕይወትንም ያጠፋሉ—2 ጢሞ. 2፥18።

መ. አማኞችን ከክርስቶስ እና ከቤተ ክርስቲያን ማዕከላዊ መንገድ ጠራርገው የሚወስዱ ነፋሳት የሚሆኑት ትምህርቶች የክርስቶስን አካል ለመገንባት የሆነውን የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ለማስተጓጎል ከሰዎች ረቂቅ ተንኮል ጋር በስውር ማታለሉ በሰይጣን የተነሳሱ ማታለሎች ናቸው—ኤፌ. 1፥10፤ 3፥9-11፤ 4፥14፤ 16፦
1. የሚከፋፍሉ ትምህርቶች የተደረጃጁት እና የተዘየዱት በሰይጣን ነው፣ ይህም ከባድ ስህተትን ለመፍጠር እና የአካሉን ሕይወት ተግባራዊ አንድነት ለማጥፋት ነው—ቁ. 3።
2. የረቀቀው ተንኮል ከሰዎች ነው፣ የስህተት ዘዴ ግን ከሰይጣን ሲሆን የቅዱሳንን ትኩረት ከክርስቶስ እና ከቤተ ክርስቲያን ዘወር ለማድረግ በክፋው በዝርዝር ከታቀዱ አታላይ ትምህርቶች ጋር ይገናኛል—ቁ. 14፤ 5፥32።

ሠ. የትምህርት ነፋሳት ዓላማ—ጠላት የሆነው የሰይጣን ክፉ ዓላማ—የክርስቶስን ሕይወታዊ አካል ግንባታ ለማስተጓጎል እና የክርስቶስን ሕይወታዊ አካል ብልቶች ለመከፋፈል፣ የክርስቶስን አካል አንድነት በፍቅር እና በርኅራኄ በመጠበቅ ፈንታ ፍጻሜ የሌለው ክፍፍሎችን የሚፈጥር ነው—1 ቆሮ. 1፥10-11፤ ይሁ. 19።

ረ. የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ የራስ አገዛዝ ነጻነትን በተመለከተ የተሳሳተ ትምህርት ወደ ጌታ ምለሳ ውስጥ ሾልኮ ገብቷል፦
1. አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሙሉ በሙሉ የራስ አገዛዝ ነጻነት እንዳላቸው ማስተማር የክርስቶስን አካል መከፋፈል ነው—ሮሜ 12፥5፤ 16፥17።
2. የራስ አገዛዝ ነጻነትን በተመለከተ ያለው ትምህርት ክርስቲያኖችን አበላሽቷል፣ ወደ ስህተት መርቷል፣ አታልሏል፣ ብዙ ክፍፍሎችንም ፈጥሯል—ይሁ. 19።
3. ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት፣ እንደ የክርስቶስ አካል የቤተ ክርስቲያን የትኛውም ክፍል የራስ አገዛዝ ነጻነት ያለው መሆን አይችልም—1 ቆሮ. 1፥2፤ 12፥12-13።
4. አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ለክርስቶስ አካል መገለጥ ናቸው፤ እነርሱ በልዩ ልዩ አጥቢያዎች የክርስቶስ አካል መገለጥ ናቸው—1፥2፤ 12፥27።
5. በአሳባችን አካሉ አንደኛ መሆን አለበት፣ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ ሁለተኛ መሆን አለባቸው—ኤፌ. 2፥21-22።
6. አካሉን የምናውቅ እና ለአካሉ ንቃተ-ሕሊናዊ ግንዛቤ ያለን ከሆንን፣ ቤተ ክርስቲያን እንደ የክርስቶስ ሕይወታዊ አካል ከራስ አገዛዝ ነጻነት ጋር ምንም ጉዳይ እንደሌላት እንገነዘባለን።

© 2021 Living Stream Ministry